# ጣልቃ የገባው ማን ነው?

ከሲኢድ መሐመድ 7/17/12

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝች በጋራ የሚኖሩባት አገር ነች፡፡ በቀደሙት ስርዓታት የብሄር ብሄረሰችና ህዝቦች እኩልነት ማረጋገጥ የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ አንዱ በሌላው የበላይነቱን የሚያውጅበትና የሁሉም ዜጎች ተጠቃሚነት ያልተረጋገጠበት ሁኔታ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው፡፡ የኋይማኖት እኩልነትና ነጻነት የሚባል ቃልም ተሰምቶ አይታወቅም ነበር፡፡ በተለይ የደርግ ሥርዓት ማንኛውንም ኋይማኖት የማጥፋት አቅጣጫ ይከተል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከደርግ በፊት የነበሩት ስርዓታትም የሃይማኖት መንግስታት እንደነበሩ የኋይማኖት እኩልነት የተረጋገጠበት ወቅት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ በአገሪቱ የነበረው የተለያዩ ኋይማኖት አማኞች መቻቻልና መተሳሰብ ግን ለዘመናት መዝለቅ የቻለ አኩሪ ባህል እንደሆነ ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ያለው ኋይማኖታዊ ቁርኝንት የጠበቀ ነው፡፡ የአንድ ሃይማኖት አማኞች ከሁሉም ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች የተውጣጡ ናቸው፡፡ በሃይማኖት አማኞች ዘንድ ዘር፣ ብሄር ወይም ቀለም መሰረት ያደረገ ልዩነት የሚፈጥርበት እድል ጠባብ ነው፡፡ ሁሉም ፍጡር ከእግዚአብሄር ወይም ከአላህ የመጣ ነው ብለው ስለሚያምኑ የሃይማኖት ተከታዮች በሰዎች መካከል የሚፈ

ጥሩት ልዩነት የለም፡፡ የአንድ እምነት ተከታዮች የበለጠ የመቀራረብና የመረደዳት ሁኔታ ቢኖራቸውም የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችን ያከብራሉ፡፡ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት ከምትለይባቸው ነገሮች አንዱ በአገሪቱ ለዘመናት የዘለቀው ሃይማኖታዊ መቻቻል፣ መረዳዳትና አብሮነት ነው፡፡

በአገሪቱ የሃይማኖት ነጻነት ባልተረጋገጠበት ወቅት ሳይቀር ኢተዮጵያውያን በኋይማኖት ልዩነት ምክንያት በጋራ ለመኖር ያስቸገራቸው ወቅት እንደሌለ ይታወቃል፡፡ መቻቻልና መተሳሰብ ለዘመናት የዘለቀ አኩሪ ባህላቸው ነው፡፡ አንዱ የሌላውን ሃይማኖታዊ ዝግጅትና ስርዓት ላይ ይገኛል፡፡ በሃዘንም ሆነ በደስታ ይተጋገዛሉ ይደጋገፋሉ፡፡ ይህ ለዘመናት የዘለቀ የኢትዮጵያውያውያን መገላጫ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎችና ሙሁራን ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡

ለዘመናት የዘለቀውን መቻቻል፣ መተሳሰብና አብሮነትን ለመናድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለው የጽንፈኞች እንቅስቃሴ ፈጽሞ ኋይማኖታዊ ተልእኮ የሌለውና ከህዝቡ ባህል የወጣ ድርጊት ነው፡፡

በእነዚህ ህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ በተሰገሰጉ የከሰሩ ፖለቲከኞች እየተፈጸመ ያለው ተግባር መቋጫ የሚሻ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

አክራሪዎቹ የእስልምና ሃይማኖት አማኞችን እርስ በርሳቸው፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችን ከክርስትና ሃይማኖት አማኞች ጋር ለማጋጨትና በመጨረሻም ሰላምን የማደፍረስ ተልእኮ ለማሳካት እየጣሩ ይገኛሉ፡፡ የሃይማኖትን ለምድ ለብሰው የጥፋት አጀንዳቸውን እውን በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡፡

በውጭና በአገር ውስጥ የሚኖሩ የከሰሩ ፖለቲከኞች ተባብረው የፈጠሩትን የሁከት አጀንዳ ዳር ለማድረስ አግባብነት በሌለው መንገድ መንግስትን ከሃይማኖት ከእስልምና አምነት ተከታዮች ጋር ለማጋጨት የተለያየ ቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ እያሰራጩ ነው፡፡ ‘መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ እየገባ ነው” በማለት ህዝበ ሙስሊሙን ለማወናበድ እየተወራጩ ይገኛሉ፡፡ መንግሥት ሕገ-መንግሥቱን እየጣሰ ነው በሚል ይወነጅላሉ፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ያቀረበውን ጥያቄ መመለስ አልፈለገም በሚልም ይኮንናሉ፡፡

ለመሆኑ መንግስት ሕገ-መንግሥቱን የሚያከብረው ለማን ሲል ነው? ሕገመንግስቱ እንዲከበር የሚያደርገውስ ለምንድን ነው? መንግስት ሕገመንግስቱን የማክበርና የማስከበር ሃላፊነት በህዝብ ስለተሰጠው ነው፡፡ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሕገመንግስቱን የማክበር አደራ በመሰጠቱ ነው፡፡ በርካታ ዜጎች ለዚህ መብት መረጋገጥ ሲሉ ተሰውተዋል፡፡ ያ ድካማቸው ከንቱ እንዳይቀር ነው መንግስት ሕገ-መንግሥቱን የሚያከብረውና የሚያስከብረው፡፡ በመሆኑም መንግስት አንድን ቡድን ለመጥቀም ሌላውን ለመጉዳት በሚል ሕገ-መንግሥቱን የሚሸራርፍበት ሁኔታ የለም፡፡

በአገራችን የሃይማኖት ነጻነት በአስተማማኝ መልኩ ተረጋግጧል፡፡ ማንኛውም ዜጋ ያለምንም መሸማቀቅ በነጻነት የፈለገውን ሃይማኖት ማመን ይችሏል፡፡ ማንኛውም የእምነት ተከታይ እምነቱ የሚጠይቀውን ተልእኮ ያለምንም ስጋት መፈጸም የሚያስችለውን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ተጎናጽፏል፡፡

በአገሪቱ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሃይማኖት ነጻነት ጥያቄ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህንን ከመሰለ ‘ነጻነት’ እየተባለ የሚዘመርለት ምንድን ነው? “ነጻነት’ እየተባለ ያለው የሌሎችን ሃይማኖት ማስቆምና ያለማስቆም ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎች አማኞች በሃይል አንድን እምነት እንዲከተሉ የማድረግና ለዚሁ ያለመተባበር እንቅስቃሴ ነው፡፡ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት ለህዝብ የሰጠውን መብት በመሸርሸር ዙሪያ ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ሆነ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች በሰላም ሃይማኖታዊ ተልእኳቸውን እንዳያከናውኑ ብጥብጥና ሁከት በዝምታ በማየትና ባለማየት ነው፡፡ መንግሥት ሰላም ሲደፈርስ ለምን እጁን አጣጥፎ አያይም የሚል ነው፡፡ መንግሥት ኋይማኖት ላይ

እጁን አስገባ የሚባለውም ከዚህ አንጻር ሆኖ በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠውን መብት ትርጓሜን እያዛቡ የማቅረብ ነው፡፡

'መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም" ማለት ምን ማለት ነው? የዚህን ሐሳብ ትርጉም አዛብቶ በማቅረብ ህብረተሰቡን ለማደናገር ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፤ ጽንፈኞቹ፡፡

መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም ማለት አማኞች እምነታቸውን በሚመለከት በሚያደርጉት ማንኛውም እንቅቃሴና ተግባር እንዲገታም ሆነ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ማንኛውን ተግባር አይፈጽምም ማለት ነው፡፡ ይህንን እመኑ ይህንን አትከተሉ አይልም፤ አንዱን ትክክለኛ ሌላውን ስህተት ነው ብሎ አያውጅም አይፈርጅም ማለት ነው፡፡ አንድ ሃይማናት አይኖረውም፤ ሁሉንም ሃይማኖቶች ለመንግስት እኩል ናቸው ማለት ነው፡፡

ሃይማኖት በመንግስት ጣልቃ አይገባም ማለት ደግሞ የአንድ ሃይማኖት አማኞች በመንግስት ተግባራት ላይ ጣልቃ አይገቡም ማለት ነው፡፡ መንግሥት ሊፈጽማቸውና ሊሰራቸው በሚችሉ ተግባራት እየገባ ለማኮላሸት የሚያደርገው እንቅስቃሴ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ተልእኮ የሚፈጸምበት ሥፍራ ሃይማኖታዊ ተግባሩን መፈጸም እንጂ መንግሥትን የሚመለከት እንቅስቃሴ አያደርግም ማለት ነው። የእምነት ሥፍራና በእምነት ምክንያት የተሰበሰቡ እማኞችን ለፖለቲካ ተግባር መጠቀም የለበትም ነው፡፡ በሃማኖት ሥፍራ ፖለቲካ አይሰበክም፣ ከመንግሥት ተግባራት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትም አይፈጸሙም ማለት ነው፡፡

ሃይማኖት እንደነዚህ አይነት ተግባራትን እንዳይፈጽም ሕገ-መንግሥቱ ይደነግጋል። መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም፤ሃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም" የሚለው አንቀጽ ሲተነተን ይህንን ይመስላል፡፡ እንዘደዚህ ከሆነ ጣልቃ እየገባ ያለው መንግስት ወይስ ሃይማኖት ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሁለቱም በየፊናቸው እያደረጉ ያሉትን መመልከት የግድ ይላል፡፡

መንግስት እያደረገ ያለው ምንድን ነው? የሚለውን እንይ፡፡ ከእስልምና ሃይማኖት አማኞች በሚል የተወሰኑ ጥያቄዎች ለመንግሥት ይቀርቡለታል፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል መጅሊሱ ይውረድልን እና የአል-አህብሽ አስተምህሮ ይቁምልን የሚሉ ይገኙበታል፡፡መጅሊሱ ህዝበ ሙስሊሙን መወከል ካልቻለ የእስልምና ሃይማኖት አማኞች ምርጫቸውን ማድረግ እንደሚችሉና የፈለጉትን የመምረጥ መብታቸው የተከበረ እንደሆነ በማስረዳት ጥቄውን እንደተቀበለው ይገልጻል፡፡ የአልአህብሽ አስተምህሮን መንግሥት ያስቁምልን የሚለው ጥያቄ ግን ተገቢነት እንደሌለው ይገልጻል፡፡ የዚህ እምነት ተከታይ የሃይማኖት ተልእኮ ይቁም የዚያኛው ይቀጥል፤ ይህ ሃይማኖት ትክክል ነው ያኛው ስህተት፤ የዚህ እምነት ተከታዮች በነጻነት ያስተምሩ የዚያኛው አሰተምህሮ ይቁም የሚል ውሳኔ ለመስጠት ሕገ-መንግሥቱ አይፈቅድም፡፡ ሕግን አክብረው በሰላማዊ መንገድ ሃይማኖታዊ

ተልእኳቸውን መፈጸም ይችላሉ፡፡ የአንዱን እምነት ተከታዮች ጥያቄ ለመመለስ የሌላውን እምነት ተከታዮች መብት ማፈን ግን ተገቢነት እንደሌለው ያስረዳል፡፡

ሌላው ከአወሊያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አወሊያ  የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከአረብ አገራት የተለያዩ ድርጅቶች ነው፡፡ በአወሊያ ስም የሚመጣው ገንዘብ በትክክል ስራ ላይ ቢውል በመላ አገሪቱ በርካታ የአዲስ አበባውን አወሊያ የሚያካክሉ ኮሌጆችን በማስፋፋት ህዝበ ሙስሊሙን ተጠቃሚ ማድረግ በተቻለ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ገንዘቡ ለግለሰቦች ሃብት ማድለቢያ መዋል ከጀመረ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህ ገንዘብ የአገር ገንዘብ የህዝበ ሙስሊሙ ገንዘብ መሆኑ ቀርቶ የጥቂቶች ገንዘብ ሆኗል። ለፈለጉት ጉዳይ ይጠቀሙበታል። መንግሥት ይህ በህዘበ ሙስሊሙ ስም የሚመጣው ገነዘብ ለመጣለት አላማ ይዋል የሚል እምነት ነው፡፡

ከአወሊያ ጋር ተያይዞ ተያይዞ እየተነሳ ያለው ጉዳይ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ አሁን በኃይማኖት ሽፋን እየተንቀሳቀሱ ካሉት መካከል አወሊያን የሚያስተዳድሩ ሰዎች   በአወሊያ ስም ሰፋፊ ቦታወችን ለትምህርት ማስፋፊያ  በሚል ሽፋን ተረክበው ለባለሃብቶብ በስውር  እየሸጡት መሆኑ ተደርሶበታል የሚል ነው፡፡ ከሃይማኖታዊ ተግባር  የወጣ ተግባርም ዓይኑን እያፈጠጠ መጣ፡፡ ኪራይ ሰበሳቢነት በመዋጋት ላይ ያለው መንግሥትም ይህ ተግባር ሊቆም ይገባል፤ በህዝበ ሙስሊሙ ስም የሚመጣው ገንዘብ በአግባቡ  ለህዝበ ሙስሊሙ የሚደርስበት መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ በመጠቀም የተቋሙ ሃላፊዎች  በራሳቸው መንገድ እንዲፈቱት አሳሰበ፡፡

በአንጻሩ ጥቂት የእስልምና ሃይማኖት ጽንፈኞች መንግሥት የህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም  የሚል አዋጅ ማወጅ ጀመሩ፡፡ በየሰፈሩና በየመስጂዱ እየዞሩ ከማስተማር አልፈው በራሪ ወረቀቶችን እያዘጋጁ መንግስትን ለማጥላላት ከፍተኛ እንቅስቃሴ አደረጉ፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ከፈጣሪው ጋር በሚገናኝበት በተቀደሰው የእምነት ቦታ የሚሰበሰብበትን ጊዜ እየጠበቁ ሁከትና ብጥብጥን ለመፍጠር በተለያየ ጊዜ ተንቀሳቀሱ። በመስጂዶች  የሚያስተምሩ የአል አህባሽ ሃይማኖት ተከታዮችንም ማሳደድ ተያያዙት፡፡ በመጅሊሱና በአህባሽ የእስልምና እምነት ላይ በሰፊው ዘመቱ፡፡ ህዝበ ሙስሊሙን ለመከፋፈልና የእርስ በርስ መቋጫ የሌለው ግጭት ውስጥ ለማስገባት  ሰፊ ጥረት አደረጉ።

መንግስት መጅሊሱ እንዳይወርድ ይፈልጋል ሲሉም ኮነኑ፡፡ የአህባሽ አስተምህሮ ለማቆም ፈቃደኛ አልሆነም በሚልም ዘመቻቸውን ቀጠሉበት። በእያንዳንዱ መስጂድ ህዝበ ሙስሊሙ በሰላም የሃይማኖት ተልእኮውን እንዳይፈጽም ሰላሙን መበጥበጥ ጀመሩ፡፡

በአገራችን የሃይማኖት ነጻነት አደጋ ላይ ነው የሚል አዋጅ አወጁ፡፡ ሰለፊያ፤ ሰውቱል እስላምና ሌሎች የግል ሚዲያወችን በመጠቀም ህዝበ ሙስሊሙን ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጉን ቀጠሉበት። የሃይማኖት ነጻነት ማለት ምን ማለት ነው? በአገራችን ያለው

ተጨባጭ ሁኔታ የሚመሰክረውስ የሃይማኖት ነጻነት መረጋገጥ ወይስ መጥፋት ነው? የሚለውን ማየት ጣልቃ የገባውን ለመለየት ያግዛል፡፡

የሃይማኖት ነጻነት በአገራችን የተረጋገጠው ለእስልምና ሃይማኖት ብቻ አይደለም፤ ወይንም ደግሞ ለክርስትና ሃይማኖት ብቻም አይደለም፡፡ ከዚያም አልፎ ለኦርቶዶክስ ወይም ለፕሮቴስታንት በሚል የታጠረ አይደለም፡፡ ለዋህቢያ ወይም ለአህባሽ የሚልም ነገር የለውም፡፡ የሃይማኖት ነጻነት የተሰጠው ለሁሉም ዓይነት ሃይማኖት በእኩል ደረጃ ነው፡፡

የእምነት ነጻነት የተሰጠውም ለህዝበ ክርስቲያን ወይም ለህዝበ ሙስሊም ብቻ አይደለም፡፡ ለኦርቶክስ አማኞች ወይም ለፕሮቴስታንት አማኞች ብቻም አይደለም፡፡ ለአህባሽ ወይም ለዋህቢያ ብቻም አይደለም፡፡ የእምነት ነጻነት የተሰጠው ለሁለም ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ሁሉም ዜጋ የፈለገውን አይነት እምነት የመከተል መብቱ ተረጋግጦለታል። ማንኛውም ዜጋ ሌላውን ዜጋ የሱን እምነት እንዲከተል ማስገደድ አይችልም። ማንኛውም ሰው እምነቱ ምንም ይሁን ምን በነጻነት ማራመድ እንደሚችል በሕገመንግስቱ ተካቷል ላለፉት ሁለት ዓስርት አመታትም ሲተገበር ቆይቷል፡፡

ይህ ሲባል የአንድ ሃይማኖት እምነት ተከታይ ተነስቶ የሌላውን ሃይማኖት የሚደፍቅበት ሁኔታ አይኖርም ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ የሚነሳ ካለ ሕገመንግስቱን መጣስ በመሆኑ ሕገመንግስቱን የማስከበር ሐላፊነት ያለው አካል መስመር ሊያስይዘው የግድ ይላል። አንድ የእምነት ተከታይ ሌሎችን ማስገደድ የራሱን እምነት እንዲከተል ለማድረግ እንዲንቀሳቀስ የሚፈቅድ አይደለም፡፡

የእምነት ነጻነት ካለ አንድ ዜጋ የሃይማኖት እምነት ሊኖረው ላይኖረው የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ የትኛውን እምነት መከተል እንዳለበትም መራጩና ወሳኙ ራሱ ነው፡፡ በማንም በሌላ አካል ተገዶ እምነት ሊይዝ አይደረግም፡፡ የኃይማኖት ነጻነት ማለት ይህ ነው፡፡ አንድ ሰው ስለራሱ እምነት በነጻነት አስቦ ተቀብሎ በነጻነት የሚያመልክበት ስርዓት ማለት ነው፡፡ አንድ አማኝ የራሱ ነጻነት እንዳይነካበት በእምነቱ ምክንያት እንዳይሸማቀቅ የህግ ከለላ የሰጠውን ሕገመንግስት ተጠቅሞ ሕገመንግስቱ ለሌሎች የሰጠውን ነጻነት ለማፈን የሚነሳበት ማለት ግን አይደለም፤ የኃይማኖት ነጻነት ማለት፡፡

አሁን በተከበረው የእስልምና ሃይማኖት ስም እየታየ ያለው ችግር መንስኤ በዚሁ የተቃኘ ነው፡፡ ጥቂት የወሃቢያ አምነት ተከታዮች የአገሪቱ ሕገመንግስት ባስገኘላቸው የሃይማኖት ነጻነት በአገራችን መንቀሳቀስና ሃይማኖታዊ ተልእኳቸውን ማከናወን ችለዋል፡፡ እነዚህ ጽንፈኛ ቡድኖች ያመጡት ዘየ ግን ከዚሁ የተለየ ነው፡፡

የአህባሽና የሌሎች የእስልምና እምነቶች አስተምህሮ መቆም አለበት ሁሉም ሰው የእኔን እምነት መከተል አለበት የሚል ነው፡፡ መንግሥት ይህንን ጥያቄ ባለማስተናገዱ ጥያቄአችንን አልተመለሰም

ይባላል፡፡ ሕገ-መንግሥቱን ማስከበር የመንግስት ግዴታ ነው፡፡ ሕገመንግስቱ ለመናድ፣ ሕገመንግስቱ ለህዝቡ የሰጠውን ነጻነት ለማፈን መሞከር በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ መግባት  ይህንን ለማስቀረት በሚጥርበት ወቅት  በሃይማኖተ ጣልቃ ገባ በሚል ህዝበ ሙስሊሙን ለማደናገር ጥረት እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ነው።  ሕገ-መንግሥቱን በመተላለፍ በመንግስት ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብተዋ፤ እነዚህ ጽንፈኞች፡፡ ሌላው ደግሞ ሰላምን ማደፍረስ ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙን እርስ በርስ በማጋጨት መቋጫ የሌለው ግጭት ውስጥ በማስገባት ሰላሙን ማናጋት። በሚሰበሰብባቸው የሃይማኖት ስፍራዎች ሁከትን በመፍጠር በሰላም ሃይማኖታዊ ተልእኮ እንዳይፈጽም  ማሰናከል፡፡

ይህ የሌሎችን መብት መጋፋት ነው። በሕገመንግስቱ የተሰጠውን የሃይማኖት ነጻነት መድፈቅ ነው። የሃይማኖት ነጻነት ለአንድ ወገን ወይም እምነት ብቻ የተሰጠ አድርጎ ማየት ጸረ ዴሞክራሲነት ነው። ሕገመንግስቱ ያረጋገጠው የሃይማኖት ነጻነት ከተጣሰ ሕግ አስከባሪው ስራውን አይሰራም ማለት ነው፡፡ ሰላም ደፈረሰ ማለት ደግሞ ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን ያለበት አካል ስራውን አልተወጣም፡፡ የሕግን የበላይነት የሚያስከብረው ደግሞ መንግሥት ነው፡፡ ሰላምና መረጋጋትን ማረጋገጥና ዜጎች በሰላም ያለምንም ስጋት የመኖር መብታቸውን ማስከበር  የመንግስት ቀዳሚ ተግባር  ነው፡፡

መንግስት በአገሪቱ ሰላም እንዳይረጋገጥ የሚያደርጉ ወገኖች ላይ ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ሃላፊበነትና ግዴታ አለበት። ከመስመር የወጣን አካሄድ ማስተካከል ይጠበቅበታል። እላይ ከቀረበው መገንዘብ እንደሚቻለው በመንግስት ጉዳይ  ጣልቃ እየገባ ያለው ጽንፈኛው ቡድን  ሆኖ እያለ መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ ገባ በማለት ህዝበ ሙስሊሙን ለማወናበድ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

መንግስት በሃይማኖት  ጣልቃ ገባ ሊባል የሚችለው መቼ ነው? ዜጎች የፈለጉትን ሃይማኖት ማመን እንዳይችሉ ሲያደርግ ነው፡፡ ዜጎች ያለፈቃዳቸው አንድን ሃይማኖት እንዲከተሉ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲኖር ነው፡፡ የሃማኖት ትምህርትንና ስብከትን ለማስቆም እርምጃዎችን  ሲወስድ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የአህባሽ አስተምህሮ ይቁምልን ለዚህ ደግሞ መንግስት እጁን ያስገባ የሚል ጥያቄ በወሃቢዎች ሲቀርብ መንግስት የሃይማኖት አስተምህሮው  እንዲቆም አድረጎ ቢሆን ኖሮ ጣልቃ ገባ ብለን ልንኮንነው በተገባ ነበር፡፡  መንግስት ግን ይህንን  አላደረገም፡፡

እያደረገ ያለው በመስጂዶች አካባቢ ህዝበ ሙስሊሙ ለጸሎት በሚሰበሰብበት ጊዜ የጸጥታ ችግር እንዳይፈጠር፣ አማኞች በሰላም ሃይማኖታዊ እምነታቸውን ፈጽመው እንዲመለሱ መጠበቅ ነው፡፡ ሁሉም የእምነት ተከታዮች የየራሳቸውን እምነት እምነታቸው በሚጠይቃቸው አግባብ ያለምንም ተጽእኖ በነጻነት  እንዲያከናውኑ ማህበራዊ ሰላምን ማረጋገጥና  ሕገ-መንግሥቱ  ያጎናጸፋቸውን የህግ ከለላ እንዳይሸራረፍ መጠበቅ ነው፡፡ ሰላምና መረጋጋትን ማስፈንና  የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ  ደግሞ የመንግስት ሃላፊነት በመሆኑ  ጣልቃ ገባ የሚያስብል አይደለም፡፡

“መንግስት በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ ሃይማኖትም በመንግስት አይገባም” ማለት የተወሰኑ የሃይማኖት አማኞች ወይም በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ወይም ግለሰብ የሕብረተሰቡን ሰላም ለማደፍረስና የህዝቡን የዕለት ተለት እንቅስቃሴ ስጋት ላይ ለመጣል እንቅስቃሴ በሚያደርግበትና የሌላውን እምነት ተከታይ አስገድዶ የራሱን እምነት በሃይል ለመጫን ጥረት በሚያደርግበት ወቅት እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል፣ በታዛቢነት ያያል ማለት ግን አይደለም፡፡ የአንድ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ከሃይማኖታዊ ተልእኮ ውጪ በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሲያደርጉና ህቡእ አጀንዳቸውን ለመፈጸም ሲንቀሳቀሱ በግድየለሽነት ያልፋል ማለት አይደለም፡፡ አንድ ሃይማኖታዊ ተቋም በሃይማኖት ትምህርት ስም በህዝቦች መካከል ሰላም እንዳይሰፍን ብጥብጥና እልቂት እንዲሰፍን የሚያደርግ ከሆነ ይህንን መስመር ማስያዝ የመንግሥት ሃለፊነት ነው፡፡ መንግሥት እያደረገ ያለውም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

ጣልቃ እየገባ ያለው በሃይማኖት ሽፋን እየተንቀሳቀሱ ያሉ ጽንፈኞች መሆናቸውን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ ይህ ጉደይ መላው የእስልምና ሃይማኖት አማኞችን አይመለከትም፡፡ መላው የእስልምና ሃይማኖት አማኞች ለሃማኖታቸውና ለሰላም ቀናኢ ናቸው፡፡ ሰላም ወዳድ ህዝብ ነው፣ ህዝበ ሙስሊሙ፡፡ ጉዳዩ ያለው በእስልምና ሃይማኖት ስም ከሚነግዱ ጥቂት ጽንፈኞች ጋር ነው፡፡ እነዚህ ጽንፈኞች በሃይማኖት ሽፋን መንግስት ጣልቃ ገባብን እያሉ ህቡእ የፖለቲካ አጀንዳቸውን እውን ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሰላምን ማደፍረስ፣ ሕገ-መንግስቱን መሸርሸርና መተላለፍ እንደዚሁም ህዝብን በህዝብ ማነሳሳትና ማበጣበጥ ሃይማኖታዊ ተልእኮ አስመስለው ይሰብካሉ፡፡ ስለሆነም ህዝበ ሙስሊሙም ሆነ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል እነዚህን የጥፋት መልዕክተኞችበጽኑ ሊያወግዛቸውና ሊታገላቸው ይገባል፡፡